# ፋኖ ማን ነው?

ሰሞኑን ስለፋኖ ብዙ ንትርክ እሰማለሁ። ብዙወች በጥሞና ላዳመጣቸው የፋኖን ምንነት ካለማወቅ እንደመነጩ ያስታውቃሉ። ከፋኖ አቅጣጫ በተለይ መንግሥት ጣቱን ቀስረብን ብለው በማመናቸው እራሳቸውን ግልጽ ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት ፋኖን ለመግለጽ ሞክረዋል። በቅርቡ በባሕር ዳር እና በምሥራቅ ጎጃም በሥልጠና ላይ የነበሩ የፋኖ አባሎች ከመንግሥት ጋር በወገኑ ኃይሎች መበተናቸው ሲሰማ የፋኖወች ሥጋት ምክንያታዊ ይመስላል። እንዲያውም ባለፉት ሁለት ቀናት ሾልኮ የወጣ የተባለ የመንግሥት ሠነድ የተወሰነ የፋኖን ክፍል ከአሸባሪወች ዘርፍ እንደመደበ ይወራል። ፋኖ ያልሆኑ አንዳንድ ግለሰቦችም ከቅንነት በመነሳት የፋኖን አገላልጽ የሚያጠናክሩ ሃሳቦች ይሰነዝራሉ። ሆኖም እነዚህ ሙከራወች በተናጠልም ሆነ በጥቅል ፋኖን በሙሉ ስለማይገልጹ የጎደለችዋን ለመሙላት ይችን አጭር ጽሑፍ ይዤ ብቅ አልኩ። የጽሑፏ ዓላማ መግባባትን በመፍጠር አስፈላጊ ወደ አልሆነ አዝማሚያ የመሄድ ዕድልን ለማመናመን ነው።

የፋኖ ጽንሰሀሳብ ከዐማራ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ቢሆንም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ዐማራ በሌሎች ማሕበረሰቦች የሚታወቀው በፋኖነት ሳይሆን በስህተት በነፍጠኝነት ነበር። ዕውነቱ ግን ዐማራ ፋኖ እንጂ ነፍጠኛ ሆኖ አያውቅም፤ ሊሆንም አይችልም። ምክንያቱን በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ። ፋኖ ዐማራ በሚጠቃበት ጊዜ አጥቂው ሊያደርሰው የሚችለውን ጥፋት ለማሳነስ ብሎም ለማቆም በቅጽበት አሰባስቦ እና አደራጅቶ የሚያሰማራው እራስ አድን (self-preservation) ኃይል ነው። በተለይ በማንነት ላይ የተመሠረተ ጥቃት በሁሉም ዐማራ ላይ ስለሚያተኩር እና እያንዳንዱ ዐማራ እራሱን እና ቤተሰቡን የመጠበቅ ተፈጥሯዊ ግዴታ ስላለበት ሁሉም ዐማራ ፋኖ ነው፤ ፋኖም ዐማራ ነው። ምንም እንኳ አብዛኛው ዐማራ ገበሬ በመሆኑ በሠላም ጊዜ አራሽ በጦርነት ወቅት ተኳሽ ይባል እንጂ ሁሉም ፋኖ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች መደበኛ ሥራ ያለው ነው። ፋኖ እራሱን የቻለ ወታደራዊ ሳይሆን ሕዝባዊ ኃይል እንደመሆኑ ነፃ እና ልል (loose) መዋቅር ኖሮት አስፈላጊ ሲሆን ቅጽበታዊ ምላሽ የሚሰጥ ኃይል ነው። ለድርጅቱ የጦር አበጋዝ፤ ለአገልግሎቱ ካሣ የለውም። የጊዜውም ሆነ የሕይወቱ ካሣው የማሕበረሰቡ ሠላም ማግኘት ነው።

የዚህ ዓይነት ኃይል በዐማራ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ማንም ማሕበረሰብ ሲጠቃ ሳይፈራገጥ አይሞትም። ስለዚህ ሁሉም ማሕበረሰብ የፋኖ ዓይነት ተፈጥሯዊ የእራስ አድን ኃይል አለው። የፋኖ አገልግሎት ወይም ዓላማው አንድ ግለሰብ ከምግብ ጋር ወይም ካለምግብ በስህተት መርዝ ሲውጥ የሰውነቱ የመከላከያ ሥርዓት (immunity system) ከሚያደርገው አጠቃላይ የመከላከያ ተግባር ጋር ይመሳሰላል። ከሥነሕይወት (biology) እንደምንረዳው ግለሰቡ መርዙን እንደዋጠ የመከላከያ ሥርዓቱ መርዙ ያልተለመደ ወይም ባዕዳ መሆኑን ተገንዝቦ ወዲያውኑ ከተለመደ ሥራው ይልቅ መርዙ የሚያደርሰውን ጉዳት በማሳነስ ቢቻልም በማስወገድ ላይ ያተኩራል። ግቡን ለመምታት ከሚያከናውናቸው ተግባሮች ውስጥ ሁለቱ መጀመሪያ በተቻለ መጠን መርዙ በተለያየ መንገድ ለምሳሌ በሽንት እና በማስታወክ ከሰውነቱ እንዲወጣ ማድረግ እና ሊወጣ ያልቻለውን ባለበት ጥፋት የማድረስ ኃይሉን ማመናመን ወይም ኒዩትራላይዝ ማድረግ ናቸው። የሰውነት የመከላከያ ሥርዓት ግቡን ከመታ በኋላ ወደ መደበኛ ሥራው ይመለሳል። ፋኖም እንዲሁ።

የዚህ ዓይነት እራስ አድን ኃይል በነገድ (tribe) ደረጃ ያሉ ማሕበረሰቦች ገጽታ ነው። በነገድ ደረጃ ማሕበረሰቦች በተናጠል እራሳቸውን የቻሉ (self-sufficient) እና ገለልተኛ ሆነው የሚኖሩ ናቸው። ሆኖም አዳዲስ ኢኮኖሚዊ ዘርፎች ለምሳሌ እርሻ፤ ንግድ፤ የእጅ ጥበብ እየተፈጠሩ የሙያ ክፍፍል ሲስፋፋ የነገድ ማሕበረሰቦች የተናጠል ኑሮ ቀስበቀስ በተጣመረ ኑሮ ይተካል። ግለሰቦችም ኑሯቸውን ለማሻሻል

ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ነገዶች ይሰባጠራሉ ይቀየጣሉ። ፖለቲካውም አዳዲስ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ሁኔታወችን ለማስተናገድ ሁሉ አቀፍ በመሆን የነገድ ፖለቲካን ይተካል። አዲሱ ማሕበረሰብ የተቀናጀ ኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን ሰፋ ያለ እና የተጠናከረ የጋራ መከላከያ ኃይልም ይኖረዋል። ይህ የጋራ ኃይል እራስ አድን ኃይሎችን (እነፋኖን) ይተካል። ለዚህ ነው እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ፋኖ ዐማራ ባልሆኑ ማሕበረሰቦች ዘንድ አለመታወቅ ብቻ ሳይሆን ለእራሱ ለዐማራው የሩቅ ትዝታ የነበረው።

ፋኖ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ትሕነግ) ተከዜን ትሻግሮ ወልቃይትን እና አካባቢዋን ከዐማራ ነጥቆ ዐማራወችን ማፈናቀል፣ መግደል። እና መሰወር በጀመረበት ጊዜ እንደገና ተከሰተ። ያም ሆኖ ላለፉት 30 ዓመታት አካባቢያዊ ሆኖ ቆይቷል። በቅርብ ጊዜ ትሕነግ ሰሜን ማሥራቃዊ ጎንደርን፣ ወሎን እና ሰሜን ሸዋን እንደሰው ሳይሆን እንደአውሎ ነፋስ (tornado) ሲያወድም እና የመንግሥት ሠላም ማስጠበቅ ችሎታ ክፍተት በማሳየቱ ፋኖ መሰባሰብ ጀመረ። መደበኛው ኃይል ሠላሙን ያስጠብቃል ብሎ በማመኑ የፋኖ መልስ ቅጽበታዊ አልነበረም። በመሆኑም ሽፍታው ትሕነግ በቆየባቸው አካባቢወች ብዙ ሰወች ገሏል፤ ጎድቷል፤ ሴቶችን ደፍሯል፤ ንብረቶችን ዘርፏል፤ መዝረፍ ያልቻላቸውን ንብረቶች እንስሳትን ጨምሮ አውድሟል። መሠረታዊ ልማቶችን ትምሕርት ቤቶችን እና የሕክምና ተቋማትን ጨምሮ አውድሟል። ባጭሩ ዐማራ ለሚቀጥሉት 20 እስከ 30 ዓመታት በዕድገት ላይ ሳይሆን መልሶ በማቋቋም ላይ እንዲያተኩር ተገዷል።

ፋኖ በአሁኑ ወቅት የመሰባሰብ እና የሙያና የአካል ብቃቱን የማጠናከር በቂ ምክንያት አለው። በጦርነቱ ቤተሰብ የሞተባቸው አዘናቸውን አልጨረሱም፤ የቆሰሉት አላገገሙም፤ የተፈናቀሉት አልተቋቋሙም፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዐማራወች እንደ ምግብ እና አልባሳት ለመሳሰሉ መሠረታዊ ቁሳቁሶች የበጎ አድራጊወችን እጆች እንዲያዩ ተደርገዋል። የወደሙት ተቋማት አልተገነቡም። አጥቂው ሽፍታ አሁንም በጋራ ድንበር አካባቢ ያሉ ቦታወችን ይዞ ሕዝቡን እያሰቃየ ነው፤ እንደ አበደ ውሻ እየተወናጨፈ በየአቅጣጫው ጦሩን እየሰበቀ እየፎከረ ነው፤ መደበኛው የሠላም አስከባሪ ኃይል ከሽፍታው አጻፋ ያላገኘ ተኩስ አቁም አውጆ ከዳር ቆሞ እየታዘበ ነው። ትሕነግ ስትንፋስ እስካለው ድረስ ድንበሮች የከርሰ ምድር እሳት ናቸው። ስለሆነም የዐማራ እና የአፋር ሕዝቦች ዘባቸውን ሊያረግቡ ዕድል አይኖራቸውም። ይልቁንም ፋኖ እና አኳያው የአፋር ኃይል ሕዝባቸውን ከትሕነግ ጥቃት ለመጠበቅ በሚያደርጉት ፍልሚያ መጣመር (ግንባር መፍጠር) እና ክንዳቸውን ቢያፈረጥሙ ከተፈጥሯዎ ኃላፊነታቸው (ሕዝባቸውን ከጥቃት መጠበቅ) ሳያፈነግጡ በተናጠል ካላቸው የላቀ ኃይል ይሆናሉ።

ከላይ እንደተጠቀሰው የፋኖ እንቅስቃሴ እራስን ለማዳን የሚደረግ እንጂ ሌላ ምኞት የለውም። እራስን የማዳን እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሚሆነው መጀመሪያ ፀረሠላም ኃይል ሲኖር ከዚያም የመደበኛው ሠላም አስጠባቂ ኃይል ኀላፊነቱን በበቂ ሁኔታ ለመወጣት ያለመቻል ክስተት ሲፈጠር ነው። በእርግጥ ፋኖ ለመዘጋጀት ዐማራው እስኪጠቃ መጠበቅ የለበትም፣ የትሕነግ አፈቀላጤ እንዳለው "በዐማራው ሂሳብ እናወራርዳለን" የሚለው ዛቻ በቂ የዝግጅት ጥሪ ነው። ዝግጁት የመደበኛ ሠላም አስከባሪ ኃይሉ ሙያዊ አፈጻጸም ላይ ክፍተት ሲከሰት ለሚያስፈልገው ተባባሪ ተግባር የመጀመሪያ ደረጃ ነው። በእንደዚህ ያሉ አጋጣሚወች ፋኖ ክፍተቱን የሚሞላ እስከሆነ ድረስ፤ የፋኖ እንቅስቃሴ ከመደበኛው የሠላም አስከባሪ ኃይል ሙያ ጋር ተደጋጋፊ እንጂ ተፃራሪ አይደለም። በመሆኑም መንግሥት ፋኖን ቢቻል ማበረታታት አለያም እንዳስፈላጊነቱ የኃይል ድጎማ ሲያደርግ ማመስገን እንጂ የሥጋት መነሻ የሚሆን ምንም መሠረት አይታየኝም።

አንዳንድ የሚንሸራሸሩ ሃሳቦች መንግሥት ፋኖን ከማመስገንም አልፎ የሆነ መደበኛ ኃይል ለምሳሌ የዐማራ ሚሊሽያ አካል እንዲያደርግ ይጠቁማሉ። ጥቆማወች በከፊል ፋኖወች ለአገልግሎታቸው ካሣ ሊያገኙ ይችላሉ ከሚል ቅን አስተሳሰብ የመነጩ ናቸው። ነገር ግን ጠቋሚወች ያልታዩአቸው ሃሳባቸውን

ተግባራዊ ለማድረግ የማያስችሉ ሁለት ችግሮች አሉ። በመጀመሪያ ፋኖ በሌላ እዝ ሥር ከገባ አስፈላጊ ሲሆን ቅጽበታዊ መልስ መስጠት አይችልም፤ ፋኖ ዋና መለያ ባሕሪውን አጣ ስለሆነም ፋኖ አይሆንም ማለት ነው። ሁለተኛ ሁሉም ዐማራ ፋኖ ነው። ስለዚህ መንግሥት ሁሉንም ፋኖ የመደበኛ ሠላም አስከባሪ ኃይል አካል ማድረግ አይችልም።

ምንም እንኳ ፋኖ የሠላም ማስከበር ሥራውን ከመደበኛ ኃይል ጋር የሚያቀናጅ ቢሆንም ነፃነቱ ቅንጂት በማይቻልበት ሁኔታ የእራሱን የሠላም ማስከበር ሥራ እንዲሠራ ያስችለዋል። ለምሳሌ ትሕነግ በተቆጣጠራቸው አካባቢወች መደበኛ ኃይሉ ለሆነ ምክንያት ሲያፈገፍግ ፋኖ መዋጋቱን ከመቀጠል አልተገታም። አሁንም የትሕነግ ትንኮሳ በቀጠለባቸው አዋሳኝ አካባቢወች ፋኖ መዋጋቱን ቀጥሏል መደበኛ ኃይሉ እንዳይተኩስ ቢታዘዝም። በሰሜን ሸዋ የተሰውት አባት እና ልጅ እራሳቸውን ለመከላከል የመንግሥትን ፈቃድ መጠየቅ አልነበረባቸውም። ስለዚህ ፋኖ ነፃ እና በሠላም ጊዜ መደበኛ ሥራውን እስካከናወነ ድረስ ልል አደረጃጀት ያለው ሆኖ መቀጠሉ አማራጭ የለውም።

ከላይ እራስ አድን ኃይሎች የነገድ ማሕበረሰቦች ገጽታ መሆናቸውን ጠቅሻለሁ። ጆሴፍ ስታሊን በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ በሚለው መጽሐፉ በብሔር ላይ የተመሠረተ (ethno-nationalism) የብሔር ጥያቄ መልስ ማሕበረሰቦች በየጎራቸው ሆነው ዘብ እንዲያቆሙ ያስገድዳቸዋል ስለሆነም ብሔራዊ ደህንነት ይዳከማል፤ ኢኮኖሚውም ይዳሽቃል ያለው ለዚህ ነበር። የስታሊን ማስጠንቀቂያወች ምን ያህል ዕውነት እንደሆኑ ያለፉት 30 ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ ምስክር ነው። በተጨማሪም ፋኖ እንደገና የተከሰተው በማንነት ላይ የተመሠረተ ጥቃት የተለመደ ክስተት እራስን የማዳን ጥሪት አስፈላጊ ስለአደረገው መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ መንግሥት የእራስ አድን ኃይሎችን ከመቆጣጠር እና ሕዝቡ አንገቱን ደፍቶ እንዲጨፈጨፍ (መንግሥት ይሄ እንዲሆን ይፈልጋል ብየ አላምንም) ከማድረግ የተሻለው እንደፋኖ ያሉ የእራስ አድን ኃይሎችን አስፈላጊ ያደረገውን የብሔር ክፍፍል ማጥፋት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። ሰሞኑን በስፋት የሚወራለት የብሔራዊ መግባባት ውይይት በዚህ ዓላማ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ ይሆናል። ምናልባት የብሔር ክፍፍል ሁሉንም ማሕበረሰቦች እንደጎዳ ማወቅ እና በአንፃሩ አማራጩ የፖለቲካ ሥርዓት የጋራ ደህንነትን (security) አጠናክሮ የእራስ አድን ኃይሎችን ተፈላጊነት ማሳጣት ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ኢኮኖሚ የመፍጠር ቀመር መሆኑን መረዳት ይጠቅም ይሆናል።

ፍትህ ለሁሉም

ጥር 23 2014 ዓ. ም.